# የአማራ ፋኖ ድምፅ
# The Voice of Fano

በወቅታዊ አርዕስት በአፋሕድ የፖለቲካ ጉዳዮች መምሪያ እየተዘጋጀ የሚቀርብ
Issued by AFPO Department of Political Affairs on Current Topics

Vol. 1; No. 3
አንደኛ ዓመት ሶስተኛ እትም

Wednesday, September 03, 2025
ረቡዕ ነሐሴ ፳፰ ቀን ፳፻፲፯ ዓ.ም.

## ርዕሰ አንቀጽ

### የፋኖ አንድነት የማይናወጥ ቃል-ኪዳናችን ነው!

አፋሕድ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የድርጅቱን የመተዳደሪያ ደንብ፣ የስነ-ምግባር ደንቦችን እንዲሁም ፍኖተ-መርህ (ማኒፌስቶ) በማዘጋጀት ከአባሎቹና ደጋፊዎቹ ጋር ውይይት አካሂዶ ገንቢ ሀሳቦችን እየሰበሰበ ድርጅታዊ አሠራርን እያጠናከረ የመጣ የሕዝብ ተቋም ነው። የአማራን የህልውና አደጋ ለመቀልበስና ጨፍጫፊውን ስርዓት ለማስወገድ መላ የአማራ ፋኖ አንድ ላይ መቆም እንዳለበት በማመን በርካታ ጥረቶችን አድርጓል። የፋኖ አደረጃጀቶችን በአንድ መዋቅር ውስጥ ለማሰባሰብ የተደከመውን ያክል ውጤት ባይመጣም አፋሕድ መሄድ ያለበትን ርቀት ተጉዟል፣ መክፈል ያለበትን ታሪካዊ ዋጋ ከፍሎ በጽናት ተሻግሯል።

አፋሕድን የገጠሙት ችግሮች አንዳንዶቹ በማይጠበቁና በማይታሰቡ መልኩ በዓላማ ልዩነት የሌላቸው የፋኖ አደረጃጀቶችና የትግሉ አካል ነን ብለው በሚያስቡ በውስጥና በውጭ በሚኖሩ አካላት መሆኑ ችግሩ ገና ከጅምሩ መሠራት የነበረበት አንድነት ግን ደግሞ በተገቢው መንገድ ባለመሠራቱ የመጣ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል። አፋሕድ ካስተናገዳቸው ችግሮች መካከል ጥቂቶቹ፡

- ድርጅቱን አፍርሶ ህልውናውን ለማሳጣት የተደረገ ብርቱ ቅስቀሳ፣
- መተኪያ በማይገኝላቸው አመራሮች እና ታጋዮች ላይ የደረሰ ጥቃት፣
- ድርጅቱ ላይ ያነጣጠሩ አሉታዊ የሚዲያ ዘመቻዎች፣
- ፋይናንስና ሎጅስቲክ እንዳያገኝ የተሰሩ እኩይ ተግባራት፣
- ያልተቋረጠ ዛቻ፣ ማስፈራሪያና ውዥንብር መፍጠር፣
- በአመራሮች ላይ የተደረገ ስም ማጣፋትና የስብዕና ግድያ ...ወዘተ ስራዎች ተሰርተውበታል።

በአጠቃላይ አፋሕድ ሁሉንም የትናንት ችግሮች በጽናት የተሻገረ ሲሆን ወደፊትም ፈተናዎችን በትዕግሥት እያለፈ፣ ስህተቶችን እና የውስጥ ልዩነቶችን በጥበብ እየፈታ ተቋማዊ አሠራርን እያዳበረ ያለ ድርጅት ነው። በተደጋጋሚ ቃል እንደገባነው ከሌሎች የፋኖ አደረጃጀቶች ጋር ግልጽነትና ቅንነት በተሞላበት፣ መርህን በተከተለ መልኩ ዘላቂ አንድነት ለማምጣት በተለይም በሌሎች የፋኖ ወንድሞቻችን በኩል በቅርቡ የታዩትን የአንድነት መነቃቃቶች እንደ ትልቅ እድል በመቁጠር የትናንት ጥፋቶችን ፍትሕ ባልተዛባበት ዕርቅና ይቅርታ በመዝጋት ሠራዊታችን፣ ሕዝባችንና ደጋፊዎቻችን የሚመኙት አንድነት እንዲመጣ በትጋት የሚሠራ ይሆናል።

#### 1. የፋኖ አንድነት

የፋኖ አንድነት የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት (አፋሕድ) የአዲስ ዓመት ቃል ኪዳን ነው። ይህን ስንል ለህልውና ትግላችን ስኬት አንድነታችን ያለውን ፋይዳ ጠንቅቀን ስለምንረዳ ነው። ስለፋኖ አንድነት በተለያዩ ግለሰቦች፣ ቡድኖች፣ እንዲሁም ድርጅቶች ብዙ ተብሏል። ይሁን እንጅ የፋኖ አንድነት ሲባል ምን ማለት ነው፣ እንዴት ሊመጣ ይችላል ለሚሉት ጥያቄዎች በቂ ማብራሪያ አልተሰጠባቸውም። የዚህ ሳምንት የአማራ ድምጽ መጽሔት አንኳር ሃሳብ ከላይ የተነሱትን ሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎች ለአንባቢያን በዝርዝር ማስረዳት ነው።

#### 2. በአንድነት ዙሪያ ከዚህ በፊት የነበሩ ክፍተቶች

ትግል ከመነሻው የሀሳብ እና የተግባር አንድነትን አብዝቶ ይፈልጋል። የአማራ ፋኖ ወደ ትግል ከገባበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ድሎችን ያስመዘገበ ቢሆንም በርካታ እንቅፋቶች አልፏል። መሆን የሌለባቸው ጥፋቶችም ተፈፅመዋል። ጠላት በሰጠን አጀንዳ እንዲሁም ኃላፊነት በጎደላቸው አባልና አመራሮች ያልተገባ መወነጃጀል፣ ስም ማጥፋትና የሀሰት ክስ፣ የራስን ከፍ አድርጎ የሌላውን ማጣጣልና ማንኳሰስ፣ በጠላት አጀንዳ መጠለፍ፣ የሌላኛውን አደረጃት ገብቶ ማፍረስ፣ ከፍ ሲልም በወንድም ላይ በመተኮስ አሳፋሪ ጥፋቶች ተፈፅመው አልፈዋል። ከአማራነት እሳቤ ወርዶ በክፍለ-ሀገርና በአውራጃ ቁመና



ለሳምንቱ ዐበይት ዜናዎች ገጽ 4ን ይመልከቱ።

For Brief News Highlights see Page 4.

መገኘት፣ ቤትን ዘግቶ ከመምከር ይልቅ ጉዳዩን ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት እና ሌሎችም የትናንት ስህተቶች ታርመው ሊሄዱ ይገባል።

#### 3. አንድነት ሲባል ምን ማለት ነው?

ከመሠረታዊ ጽንሰ ሀሳብ ስንነሳ አንድነት ማለት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በስምምነት፣ በትብብር ወይም በጋራ የሚሰባሰቡበት፣ ያልተከፋፈለና የተሳሰረ ሁኔታ ማለት ነው። ይህ ማለት የተለያዩ ክፍሎች አንድ ላይ በመሆን፣ በጋራ መሥራት መቻል ማለት ነው።

አንድነት አንደ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ ወይም ሕዝብ መረዳዳት፣ ኀዘንና ደስታን መጋራት፣ ጠላትን በጋራ መመከት፣ የአንዱን መጠቃት የሁሉም መጠቃት አድርጎ መቁጠር ማለት ነው።

አንድነት በአንድ ላይ ለመኖርና ለመልማት በጋራ ቃል መግባት ነው። የአጭር ጊዜ ግለሰባዊ ወይም ቡድናዊ ስኬትን፣ ወይም ፍላጎትን ማስላት ሳይሆን የቀጣይ የጋራ እጣ ፈንታን በጋራ መወሰን መቻል ማለት ነው። ከዚህ አንፃር አንድነት በጋራ እጣ ፋንታ፣ የጋራ ግብና የጋራ እሴቶች ላይ ተስማምቶ መሥራት መቻል ማለት ነው።

በተለይም የአማራ ፋኖ በማንነቱ የተገፋን አማራ ከጥፋት ለማዳን እስከወጣ ድረስ መሰረታዊ የአላማ ወይንም የግብ ልዩነት እንደሌለው ይታወቃል። ወደ ትጥቅ ትግል ተገዶ የገባው የአማራ ሕዝብ ህልውና አደጋ ላይ በመውደቁ ሲሆን ዋና ግቡም ይህን የህልውና አደጋ በመቀልበስ ሰላምን፣ ፍትሕና እኩልነትን ለማስከበር ነው። ይህ የፋኖ ትግል አማራን ብቻ ሳይሆን መላ ኢትዮጵያ ላይ የተንሠራፋውን ዘረኝነትና ኢፍትሃዊነት ጭምር ከወንድም የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሆኖ ታግሎ ነፃ ማውጣትንም ያለመ ነው። ስለዚህ በዚህ ግልጽ አዓማ ላይ ልዩነት የሌለው ፋኖ ጨፍጫፊ የሆነ ስርዓትን ለማስወገድና ሕዝብን ነፃ ለማውጣት አንድ መሆን የውዴታ ግዴታ ያደርገዋል።

#### 4. የአንድነት አስፈላጊነት

አንድነት አያሌ ጠቀሜታዎች ያሉት ቢሆንም በዋናነት፡-

i. **አንድነት ኃይል ነው፡-** አንድነት የጋራ ጥንካሬን ያሳድጋል። ሰዎች በተከፋፈሉ ቁጥር ደካማ ይሆናሉ። በሀገራችን የተለመደውን አባባል ማስታወስ ጠቃሚ ነው። **ድር ቢያብር አንበሳ ያስር።** የአሸናፊነት ምስጢሩ አንድነት ነው። አንድነት ካለ ጥንካሬ አለ፣ ጥንካሬ ካለ ደግሞ ማሸነፍ አለ፣

(ገጽ 2 ላይ ይቀጥላል)

## Editorial

### Fano Unity: Our Non-Negotiable Covenant!

AFPO has proven resilient and effective, tempered by more than a year of trials; allies and adversaries alike acknowledge this—some with respect, others with concern.

**A Beacon of Strength and Purpose.** AFPO attracts dedicated, capable patriots, outlasts fleeting media cycles and distractions, withstands internal and external pressures, and maintains a clear mission and steady resolve.


**A Vision Beyond Borders.** It is a long-horizon movement committed to the vitality and unity of millions—within the Amhara region, across Ethiopia, and throughout the diaspora. AFPO has navigated internal challenges with patience and maturity, keeping its doors open to all who seek unity and justice for the Amhara people.

**Internal Strength and Democratic Values.** The organization has strengthened its cohesion, addresses differences through institutional mechanisms and democratic norms, and cultivates transparency, accountability, and mutual respect.

**Defined by Structure and Engagement.** AFPO operates with clear, transparent leadership, a robust Fano framework led by recognized patriots, active engagement with diaspora representatives, and a growing presence across all sectors of the struggle.

**A Movement with a Manifesto.** Recognized internationally and embraced by many Ethiopians as a symbol of hope, AFPO has publicly shared a draft manifesto that sets out its principles and long-term vision.

(Continued on page 3)



(ከገጽ 1 የቀጠለ)

ii. **አንድነት ሠላም ነው፡-** አንድነት ግጭትን ይቀንሳል፣ መረጋጋትንና መረዳዳትን በማጠናከር የውስጥ ሰላምን ያመጣል፣

iii. **አንድነት ለውጥ ነው፡-** በጋራ ዓላማ ተሳስሮ በአንድነት መሥራት ከተቻለ ግብን በፍጥነትና በጥራት ማሳካት ይቻላል፣

iv. **አንድነት ተቀባይነትን ማሳደግ ነው፡** አንድነት በቀጠናው የተሻለ ኃይል ሆኖ ለመውጣትና የመንግስትነት ቁመናን እየተለማመደ የዲፕሎማሲ ተቀባይነት ለማግኘት ትልቅ እድል ይፈጥራል፣

v. **አንድነት ኃላፊነትን መውሰድ ነው፡-** ዓለማቀፍ ህግጋትን አክብሮና አስከብሮ ኃላፊነትን ለመውሰድና ወንጀለኛን ለማጋለጥ አንድነት በእጅጉ ጠቃሚ ነው። በተበታተነ አደረጃጀት በመካከል በሚፈጠር ችግር ወይንም ጠላት በሚፈጥረው ችግር ከፍተኛ ወንጀል እየተሠራ ተጠያቂነትን ለማስፈን በእጅጉ ከባድ ያደርገዋል።

## 2. የፋኖ አንድነት መርሆዎች

የፋኖ ታጋዮችና የአማራ ሕዝብ የህልውና ትግል ደጋፊዎች የአማራ ሕዝብን ህልውና፣ ነፃነትና ፍትሕ ቅድሚያ የሚሰጡት ጉዳይ መሆን አለበት። መከፋፈል

ትግላችንን እንደሚያዳክም፣ አንድነት ደግሞ የአሸናፊነት ቁልፍ መሆኑን ሁሉም አካል መረዳት አለበት። ለዚህም በአንድነት፣ በጋራና በመከባበር በቅንጅት ለመታገልና ትግሉን ለመደገፍ ቃል መግባት አለባቸው። በመርህ የሚመራ ትግል ጠቀሜታው ዛሬ ላይ ለሚደረገው ትግል ብቻ ሳይሆን ነገ ከትግል በኋላ ለሚመሰረተው ስርዓት ከአሁኑ የሚጀመር ስለሆነ መርህን ተከትሎ መታገል ትግሉ ግቡን እንዲመታ ወሳኝ ሚና አለው። ለዚህም ይረዳ ዘንድ የአንድነት መርሆዎችን ማውጣትና መፈጸም በጣም አስፈላጊ ነው።

### የፋኖ አንድነት መሰረታዊ መርሆዎች

i. ሁሉም አማራ ያለ ልዩነት የሚያነሳቸውን የሕዝብ ጥያቄዎች የጋራ አድርጎ መውሰድ፣

- ሁሉም ታጋይና ደጋፊ የአማራ ሕዝብን ከጭቆና፣ ከመፈናቀልና ከማንኛውም ጥፋት ለመጠበቅ መሥራት አለበት፣
- ሕዝባችን የትግላችን ህጋዊነት/Legitimate cause/ ምንጭ ነው፣ የሕዝባችን ህልውናና ክብር ከሁሉም በፊት ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳይ መሆኑን ሁሉም ታጋይና ደጋፊ ማወቅ አለበት ከዚህም በላይ የሕዝባችን ስሜትና ፍላጎት ማዳመጥ ወሳኝ ጉዳይ ነው።

ii. የጋራ እውቅና መሰጣጠት

- የትኛውም የፋኖ አባል(ቡድን) የሌሎችን የትግል መስዕዋትነት ከማጣጣልና ማንኳሰስ በመቆጠብ የትግል አጋር መሆናቸውን መመስከር፣

iii. ዋና ዋና የጋራ ግቦች ላይ መስማማት

- የአማራ ሕዝብ ህልውናን መታደግ፣ ጸረ-አማራ ትርክትን ማረም፣ ታሪካዊ ግዛቶቹን፣ ፖለቲካዊና ዲሞክራሲያዊ መብቱን ማስከበር፣
- በሕዝባች ላይ ለተፈጸመው ግፍና በደል ፍትሕና ተጠያቂነትን ማምጣት፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍትሕን የሚያመጣ ስርዓት መዘርጋት ወዘተ የትግላችን ዋና ዋና ግቦች መሆናቸውን መስማማት ያስፈልጋል፣

iv. የቅንጅትና ትብብር ባህልን ማድረግ

- ለግንኙነት፣ መረጃና ደህነንት እንዲሁም ሀብት ለማሰባሰብ ወዘተ የጋራ ሥርዓት መዘርጋት፣
- ሁሉም የፋኖ ታጋይና ደጋፊ ከጋራ ዓላማችንና ከሕዝባችን ጥቅም ጋር ከሚቃረን ማንኛውም ተግባር መቆጠብ፣

v. የጎንዮሽ ትንኮሳ እንዳይከሰት በጋራ መሥራት

- ማንኛውም የፋኖ አባል (ቡድን) በሌላውኛው ፋኖ ላይ ምንም ዓይነት ጥቃት እንዳይፈፀም የጋራ አቋም መያዝ፣
- አለመግባባቶች ሲከሰቱ በውይይት፣ በንግግር ወይም እምነት በሚጣልባቸው የሀገር ሽማግሌዎች/አባቶች/የጋራ ምክር ቤት/ እርምት እንዲወሰዱ ማድረግ፣

vi. የጋራ ውክልናን ያካተተ የፋኖ አንድነት ምክርቤትን ማቋቋም

- ወደ ምልዑ አንድነት ለመሸጋገር፣ የጋራ መግለጫዎችን ለማውጣት፣ እንዲሁም ከዲያስፖራውና ዓለም ዓቀፍ ማህበረሰቡ ጋር ለመተሳሰር ከሁሉም ወገን የተውጣጡ ተወካዮችን ያቀፈ የፋኖ አንድነት ምክርቤትን ማቋቋም፣

vii. የዲያስፖራና ዓለም አቀፍ ማህበረሰቡን ተሳትፎ ማሳደግ

- ለዲያስፖራውና ዓለም አቀፍ አጋሮቻችን የአንድነት ጥረቱን እንዲደግፉ፣ ኃብት እንዲያሰባስቡ፣ እንዲሁም ትግላችን በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እንዲያገኝ ጥረት እንዲያደርጉ ጥሪ ማቅረብ፣ ተሳትፏቸውን ማሳደግ፣

viii. ምሳሌያዊ አንድነት

- በየትኛውም አደረጃጀት ውስጥ ሆነው ሲታገሉ የተሰው ሁሉንም የፋኖ ሰማዕታት እንደ አንድ የአማራ ሕዝብ ጀግኖች አድርጎ መቁጠር፣ በጋራ መዘከር፣ ማክበር፣
- የጋራ ዓላማችንን ለማረጋገጥ የጋራ ምልክቶችን፣ መፈክሮችን፣ እንዲሁም መታሰቢያ በዓላትን ማወጅ፣

ix. ቃል ማክበር

- የአማራ ሕዝብን ህልውና ከግለሰብ፣ ቡድን ወይም ድርጅት ጥቅም በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው በመሆኑ፣ አለመግባባቶችን በውይይት ለመፍታት እንዲሁም ለሕዝባችን ህልውና፣ ነፃነትና ፍትሕ በጋራ ለመታገል ቃል መግባትና ቃልን ማክበር።

x. ብአዴን የፈጠራቸውን የአንድነት መሰናክሎች አለመውረስ

- ብአዴን የአማራ ሕዝብን ውስጣዊ አንድነት ለዘላቂው ለመናድ ሲል ያደረጋቸውን ውስጣዊ የወሰን ሽግሽጎች እውቅና መንሳት።

## 5. የአማራ ፋኖ አንድነትን ለማምጣት በጥንቃቄ የሚታዩ ጉዳዮች

እውነተኛ አማራዊ አንድነት የተላበሰ ተቋም ለማምጣት ብርቱ ሥራ ይጠይቃል። ቆራጥ የሆነ ተግባራዊ ውሳኔም ያስፈልገዋል። በአንድነት ሥራው ላይ የሚከተሉትን ጉዳዮች በጥንቃቄ ልናያቸው የሚገቡ ናቸው።

i. **ሁሉንም አደረጃጀቶች በአንድ ተቋም ማስገባት፡-** ሁሉም ሀቀኛ ፋኖ ትግሉ አሸናፊ እንዲሆን ድርጅት እንደሚያስፈልገው ያምናል። በዚህም መሠረት የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት ከአንድ ዓመት በፊት ተመሥርቶ ብርቱ ዋጋ እየከፈለ ከዚህ መድረስ የቻለ ሲሆን ከቅርብ ወራት በፊትም ከአፋሕድ ውጭ ያሉት የፋኖ አደረጃጀቶች በጋራ ሆነው አፋብኃን መሥርተዋል። እንደሚታወቀው የአማራ ሕዝብ ፈተና አታጋይ ድርጅት መስርቶ አፅንቶ የማዝለቅ ጉዳይ ነው። ስለሆነም የጋራና አካታች የሆነ ጠንካራ ድርጅት መስርቶ ተጨባጭ የለውጥ እድገቶችን ማስመዝገብ የዚህ ትውልድ ታሪካዊ አደራ ሆኖ ተቀምጧል።

ii. **ግልጽነት የሌላቸው/ጥርጣሬ የሚፈጥሩ/ አካላት፡-** የተለያዩ አደረጃጀቶች ውስጥ የነበሩ አካላት ወደ አንድ ሲመጡ ከፊት ካሉት አመራሮች ውጭ አብዛኞቹ በአካልም ስለማይተዋወቁ፤ በተለይም የፋኖ አማካሪ ሆነው የቆዩ አካላት የተለያዩ ፍላጎት ያላቸው በመሆናቸው ወደ አንድነቱ መግባታቸው አለመተማመንና የአንድነቱ ትልቅ እንቅፋት ሊሆን ስለሚችል ይህ እንዳይፈፀም አንድነቱ በጥንቃቄ ሊሠራ ይገባዋል።

iii. **የጋራ ውሳኔ ሰጭነትን ተግባራዊ ማድረግ፡-** እስካሁን በነበሩን የአንድነት ጥረቶች በከፍተኛ ሁኔታ የፈተነን ጉዳይ ከትግሉና ከወጣንበት አላማ ባፈነገጠ መንገድ ከሰብሳቢ ጀምሮ ልዩ ልዩ የሥራ መደቦችን ይገባኛል የሚለው ጥያቄ ነው። ዴሞክራሲና ነፃነት በተራቀቀበት በዚህ ዘመን የጋራ ውሳኔ ሰጭነት የሚዳብርበትና የአማራን የነፃነት ትግል በጋራ ምክክርና ውሳኔ የሚሰጥበት ህገ-ደንብ ሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል። በአማራነታችን የተሠራብንን ጥልፍልፍ አጀንዳ በውሉ ተረድተው በፅናት ማሻገር የሚችሉና ተራማጅ አማራዊ ሃሳብ ያላቸው ታማኝ አመራሮችን ወደፊት ማምጣት ተገቢ ይሆናል።

iv. **ከጎጠኘነት እሳቤ መውጣት፡-** ጎጠኝነት ብአዴናዊ እሳቤ ነው። ከኢትዮጵያዊነት ያወረደን የህወኃት የዘር ፖለቲካ ነው። ከአማራነትም ዝቅ ያደረገን በህወኃት ሳምባ የሚተነፍሰው ብአዴን ነው። ይህ በሽታ ወደ ሕዝባችን ወርዶ አሁን አሁን በፋኖ ውስጥም ገብቶ ችግር እየፈጠረ ይገኛል። ይሄ የጎጠኝነትና የመከፋፈል አጀንዳ የጠላት አጀንዳ መሆኑ ታውቆ ሁላችንም በአማራዊ እሳቤ ብቻ ልንሰለፍ ይገባል። በሠራዊታችንም ውስጥ ይሄ የጎጠኝነትና የሰፈርተኝት እሳቤም ጠፍቶ አማራዊ ወንድማማችነት እንዲዳብር ተከታታይ ስልጠናና ግንዛቤ በመስጠት ይሄን የጠላት አጀንዳ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ፋኖ ሊያከስመው ይገባል። ጎጠኝነትን ለማክሰም ከሚሠራው ሥራ ጎን ለጎን ዲሞክራሲያዊ ውክልናን ማረጋገጥ አስፈላጊ እንደሆነ ይታመናል።

v. **ሳይንሳዊ አደረጃጀት ያለው መዋቅር መዘርጋት፡-** የትግላችን አላማ ስርዓት ነቅለን ለሀገር የሚበጅ እውነተኛ ስርዓት ማንበር ነው። ብርቱ መሰዋዕትነት እየከፈልን ከዚህ ያደረስነውን ትግል በደካማ ጎናችን ገብተው ሴረኞችና ክፉ ጠላቶቻችን ዛሬም ዕረፍት አልባ እየሠሩ ይገኛሉ። ለዚህም ዘመኑን የዋጀና በሁሉም ዘርፍ እምርታ ሊያመጣ የሚችልና አዳጊ የሆነ ተቋም መዘርጋት ያስፈልጋል። የፋኖ አደረጃጀት ከባህላዊና ኃላቀር አሠራር ተላቆ የዘመኑን የረቀቀ ወታደራዊ ሳይንስና የቀጠናውን የኃይል አሰላለፍ እንዲሁም የነጻነት የትግል ድርጅትን ውስብስብ ባህሪያት (military & political dynamics) የሚረዳ አደረጃጀትና የፖለቲካ ሴራውን መተንተንና መረዳት የሚችሉ ታጋዮች ትግሉን የሚቀላቀሉበት ሁኔታ መፈጠርና የትግል አድማሳችን ማደግ መቻል አለበት።

vi. **የጠራ የትግል መስመርና አላማ፡-** ጨፍጫፊው ስርዓት ትግላችንን ለመጥለፍና ከሌሎች ጋር ለማጋጨት ከሚሄድበት መንገድ አንዱ የሃይማኖት አጀንዳ ነው። እምነትን ከግላዊ የሕይወት መርኅነት አሳልፎ ከፋኖ አደረጃጀት ወይም አሠራር ጋር በማያያዝና ትግላችንን ከእምነት ጋር አያይዞ ለመፈረጅ ጠላት ብዙ ጊዜ ሙከራ እያደረገ ይገኛል። ይህን ፍረጃ ወደ ፋኖ ትግል የሚያመጡ አካላት ካሉ ከጠላት ተለይተው የሚታዩ አይሆንም። ይህን የጠላት አጀንዳ የምናከሽፈው በጠራ መስመር ላይ ብቻ የተመሰረተ ትግል ይዞ በመቀጠል ነው። የአማራ እሴት፣ እምነት፣ ታሪክ፣ ትውፊት ወዘተ አብረው የጥቃቱ ሰለባ ቢሆኑም የጋራ ማንነታችንና ለጥቃት ያጋለጠን ግን አማራነታን መሆኑን በመረዳት የጠራ አላማ ይዞ መራመድ ይገባል።

vii. **የተሠሩ ጥፋቶችን በዕርቅ ስለመዝጋት፡-** ፋኖ ከመሰረቱ ተቋም መስርቶ የወጣ ሳይሆን ሁሉም ለህልውናው ወጥቶ ሜዳው ላይ የተገናኘ በመሆኑ በየአካባቢው ባለ አደረጃጀት ውስጥ ገብቶ እየታገለ ቆይቷል። በዚህ የአደረጃጀት ልዩነት ምክንያት ጠላት ሰርጎ በመግባት ከራሳችን ደካማ

ጎን ጋር ተዳምሮ እርስ በእርስ የመጠላለፍ ከፍ ሲልም በወንድሞቻችን ላይ ምላጭ ስበን ማጣት የሌለብንን ወንድሞቻችን አጥተናል። ይህ ጉዳይ ወደፊት ቁስል ሆኖ እንዲቀጥል አይፈለግም። ይህንና ሌሎችንም ልዩነቶቻችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በእውነተኛ ዕርቅና ይቅርታ፤ እንዲሁም ባለፉ ወንድሞቻችን ቤተሰቦች ካሳ ፋይሉ ተዘግቶ የተሰው ወንድሞቻችን ራዕይ ማሳካት የሠራዊታችን፣ የሕዝባችን፣ የደጋፊዎቻችንና በጥቅሉ በቀጠናው ሰላምና ፍትሕ እንዲሰፍን የሚፈልጉ አካላት ሁሉ ጽኑ እምነት ነው።

viii. **የሚዲያ አጠቃቀም፡-** ሚዲያ ለትግላችን አወንታዊ አበርክቶ እንዳለው ሁሉ የጠላት የሚዲያና ሳይበር ሠራዊት ስምሪትም በከፍተኛ ደረጃ ጉዳት አምጥቷል። የጠላት የሚዲያ ሠራዊት በተለያዬ መልክና ቁመና ተመሳስለው ገብተው ትግላችን በተለይም የጨፍጫፊው ስርዓት ራስ ምታት የሆነውን የፋኖን አንድነት ለማደናቀፍ ያለእረፍት እየሠሩ ይገኛሉ። ድምጽን ቆርጦ በመቀጠል የአንዱን ወገን የደገፉ መስለው ከሌላኛው ጋር ለማጋጨት የሴራ ተግባራቸውን በሰፊው ተያይዘውታል። ለዚህ የጠላት አፍራሽ ተልዕኮ ከወዲሁ አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጎ በሁሉም የፋኖ አደረጃጀቶች የጋራ ምላሽ መስጠትና ማምከን ያስፈልጋል። ለትግሉ ጠቃሚ መስለው ነገር ግን ለግል ጥቅማቸው የፋኖ አመራሮችን ተራ በተራ እያነጋገሩ ጣት የሚያቀሳስሩ አሠራሮችን ለማስቀረት የተጠና አሠራር እና የሕዝብ ግንኙነት መፍጠር።

ix. **ማኒፌስቶ (ፍኖተ-መርህ)፡-** አፋሕድ እንደ ድርጅት ሕዝባዊ ውይይት ተደርጎበት በመፅደቅ ሒደት ላይ የሚገኘውን የማታገያ ሰነድ (ማኒፌስቶ) አንድነቱ ሲመጣ እስካሁን ባልገመገሙት ወንድሞቻችን ተተችቶና እንዲዳብር ተደርጎ የትግል ሰነድ ሆኖ እንደሚቀጥል ይጠበቃል።

x. **ዲፕሎማሲና የውጭ ግንኙነት፡-** በዚህ የአንድነት ሒደት አደረጃጀቶች የጀመሩት የውጭና የሀገር ውስጥ ግንኙነት ካለ አንድነቱ በሚፈፀምበት ወቅት ግልፅ መደረግ አለባቸው። ይህ የዲፕሎማሲና የትብብር ጉዳይ ከአንድነት በኋላ በጥናት ላይ ተመስርቶ የሚወሰን ይሆናል። ለምሳሌ የአማራን ሕዝብ ታሪካዊ ጠላቶችና እንደ ሀገር ሊጎዳ የሚችል ቋሚ ፍላጎት ያላቸው ሀገሮችና ድርጅቶች ጋር የተደረገ ግንኙነት/ስምምነት/ ካለ ሊቋረጥ ይገባዋል።

xi. **የውጭ አስተባባሪ ኮሚቴ አወቃቀር፡** በሌላ በኩል በውጭ ሀገር የሚኖረውን የአማራ ተወላጅና ደጋፊ የትግሉ ባለቤት ሆኖ እንዲቀጥል ውህደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በአዲስ መልክና አሠራር ተዋቅሮ አቅም እንዲሆን ማድረጉ የተሻለ መተማመን ይፈጥራል።

ድል ለአማራ ሕዝብ!

ሰላም ለኢትዮጵያ!

ረቡዕ ነሐሴ ፳፰ ቀን ፳፻፲፯ ዓ.ም.
ኢትዮጵያ።

(Contiued from page 1)

AFPO continues to grow in size, quality, and capability, remaining steadfast in strengthening the vitality and resilience of the Amhara people, enduring trials with patience and resolve, and addressing differences and past missteps with integrity.

**Commitment to Unity.** In concert with other Fano structures, AFPO remains open to unity grounded in transparency, honesty, and shared principles, reaffirming its commitment to a unified, clearly guided, and principled common front.

🔷 What Is Fano Unity?

Fano unity is the New Year's covenant of the Amhara Fano People's Organization (AFPO). It affirms that unity is essential to the success of our struggle. While many individuals and groups have spoken about Fano unity, few have defined what it truly means or how it can be achieved. This week's edition of The Voice of Fano seeks to answer two foundational questions:

- What does Fano unity mean?
- How can it be realized?

⚔️ Previous Obstacles to Unity

From the beginning, our movement has aspired to unity in thought and action. Despite many victories, the Amhara Fano struggle has faced internal fragmentation and setbacks. These include:

- Reckless accusations and character assassinations
- Ego-driven rivalries and infiltration by enemy agendas
- Regionalism and outsourcing internal disputes to third parties
- Attacks among brothers and the erosion of mutual trust

These obstacles to unity must be acknowledged and addressed. We must move forward with reconciliation and clarity.

🧭 What Does Unity Mean?

Unity means individuals or groups coming together in agreement, cooperation, and shared purpose. It is the opposite of division. Like a family or community, unity involves:

- Sharing joy and sorrow
- Defending against common enemies
- Treating harm to one as harm to all

Unity is not merely a slogan—it is the act of coming together in shared purpose, agreement, and cooperation. It is the decision to live and grow as one. True unity is not driven by short-term personal or group success, nor by fleeting interests. It is the ability to jointly define and pursue a long-term, collective mission.

From this perspective, unity means working together based on shared goals, mutual responsibility, and common values. Especially for the Amhara Fano movement, which rose to rescue the Amhara people from existential threat, there is no fundamental difference in purpose or mission. The movement was born out of necessity—to protect a people on the brink of destruction.

The Amhara people entered this struggle because their survival was at stake. The central goal is to overcome this danger and establish peace, justice, and equality. This is not a struggle for Amhara alone. It is a broader fight against systemic oppression and injustice across Ethiopia. It is a struggle carried out in solidarity with all Ethiopians—to dismantle entrenched ethnic discrimination and liberate the nation.

In pursuit of this clear and noble goal, unity is not optional. It is a moral obligation. To dismantle the oppressive regime and liberate the people, standing together as one is a sacred duty. Fano must rise not as fragmented voices, but as a unified force committed to freedom, dignity, and national renewal.

🛡️ Why Unity Is Essential

Unity brings:

- Strength: "United spider threads can bind a lion". United, we are powerful.
- Peace: Unity reduces conflict and fosters internal stability.
- Progress: Shared goals accelerate change.
- Legitimacy: Unity enhances diplomatic recognition and influence.
- Accountability: Unity enables justice under international law.

📜 Fano Unity Principles

All Fano fighters and supporters must prioritize the survival, freedom, and justice of the Amhara people. Division weakens us. Unity is the key to victory. Every faction must commit to coordinated and principled action.

🔟 Ten Foundational Principles of Fano Unity

1. Stand for common Amhara interests – Protect the Amhara population above all.
2. Mutual Recognition – Respect each group's contribution to the struggle.
3. Shared Goals – Defend Amhara identity, historical territories, and rights.
4. Collaborative Culture – Build systems for communication, security, and resource sharing.
5. Prevent Infighting – Resolve disputes peacefully through dialogue and elders.
6. Joint Council – Establish a representative Fano Unity Council for coordination and diplomacy.
7. Diaspora Engagement – Mobilize global support and resources.

8. Symbolic Unity – Honor fallen heroes collectively and promote shared identity.
9. Honor Commitments – Uphold promises made in the name of the people.
10. Reject Divisive Regime Legacies – Distance from past political agendas that sowed division.

🧠 Strategic Imperatives

To build true unity, we must:

- Consolidate all organizations under one umbrella
- Avoid unclear or manipulative actors
- Establish democratic decision-making structures
- Promote trustworthy leadership
- Eliminate divisive ideologies and external agendas
- Develop a scientifically structured organization
- Maintain a clear and focused agenda for the struggle
- Close the chapter on past mistakes through reconciliation
- Strengthen media strategy to resist misinformation

🌐 Diplomacy & Diaspora Coordination

- A unified manifesto is being finalized through public consultation.
- Diplomatic and international relations must be clarified post-unity.
- Any existing ties with historical enemies or harmful foreign interests must be reconsidered.
- A new diaspora committee will be formed to support the struggle with resources and advocacy.

Victory to the Amhara People!

Peace for Ethiopia!


September 03, 2025.

Ethiopia.

## የሳምንቱ ዐበይት ዜናዎች

❖ **አዲሱ ዓመት የፋኖ የአንድነትና የድል ዓመት እንዲሆን ጥሪ ቀረበ።**

የአፋሕድ ሊቀመንበር አርበኛ እስክንድር ነጋ የ2018 አዲስ ዓመትን አስመልክቶ ባወጡት የአንኳን አደረሳችሁና የአንድነት ጥሪ የአማራ ፋኖ ትናንት የተሠሩ ስህተቶችን ለፈጣሪና ለታሪክ ትተን የአንድነት ቃልኪዳናችን በማደስ ትግላችን ወደ ላቀ ደረጃ አድጎ መንግሥታዊ ቁመና መያዝ እንደሚጠበቅብን አሳስበዋል። ከዚህም ባሻገር አንዳንድ የመረጃ ምንጮች እንደጠቆሙት የፋኖ አመራሮች አንድ መሆን የምንችለው በሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ሳይሆን በእኛው በራሳችን ነው በማለት የአፋሕድና የአፋብኃ አመራሮች መልካም የሚባል ግንኙነት እያደረጉ እንደሆነ ተጠቁሟል።




**የብልጽግና ሠራዊት ገና ከስልጠና ወጥቶ ወደ ግዳጅ ሲሄድ መንገድ ላይ እየሾለከ እየጠፋ ነው።**

የአብይ አህመድ አምባገነን መንግስት መደበኛ ሠራዊቱን በውጊያ ተመናምኖ ሲያልቅበት ከሀገሪቱ ሁሉም ክፍሎች እያፈሰ ወስዶ በተለያዩ ማሰልጠናዎች ለስልጠና ቢያስገባም በየቦታው ሠራዊቱ የፋኖን ምት መቋቋም ሲያቅተው አፍሶ ያስገባቸውን ስልጠናቸውን ሳያጠናቅቁ መለዮ ብቻ በማልበስ ወደ ግዳጅ ቢላኩም ገና በምንገድ ላይ መሹለክ የጀመሩ ሲሆን ወደ ግዳጅ ወረዳ እንደደረሱ በአንድ ቀን አዳር ብቻ ከ85 በላይ ከድተው ማደራቸውን፣ ከፊሉም ወደ ፋኖ የተቀላቀሉ መሆናቸውንና ምንም አይነት ውጊያ ስነ-ልቦና ዝግጅት እንደሌላቸውና አብዛኞቹም ለመውጣት በዝግጅት ላይ መሆናቸውን የመረጃ ምንጮች አረጋግጠዋል።

❖ **ለሁለት ዓመት ተቋርጦ የነበረውን ትምህርት ለማስቀጠል ምዝገባ እየተጀመረ ነው።**

አፋሕድ ለሁለት ዓመት ተቋርጦ የነበረውን ትምህርት ለማስቀጠል በገባው ቃል መሰረት በርካታ በየዕዙ ስር ያሉ በርካታ ክፍለጦሮች የሕዝብ ውይይት፣ የትምህርት ቤት ጥገና፣ እንዲሁም የተማሪ ምዝገባ እየተካሄደ ይገኛል። በተማሪዎች፣ ወላጆችና መምህራንም ከፍተኛ የሆነ ድጋፍና ተነሳሽነት ታይቶበታል። ሆኖም አንዳንድ ትምህርት ቤቶች በደረሰባቸው ከፍተኛ ብልሽት ከማህበረሰቡ ተሳትፎ ባሻገር የበርካታ አጋር አካላትን ትብብር የሚጠይቁ መሆናቸው ተጠቁሟል።

## Brief News Highlights

🔔 A Call for Unity and Victory

As the New Year begins, a powerful call has been issued for Fano to embrace unity and triumph. AFPO Chairman, Patriot Eskinder Nega, marked the arrival of 2018 E.C. with a heartfelt message urging all factions to renew their covenant of unity. He emphasized that past mistakes—whether internal divisions or missteps—must be entrusted to history and the Creator. By reaffirming our shared commitment, he declared, the struggle can rise to a higher level and attain legitimate national stature.

⚔️ Prosperity Party Forces in Collapse

The Prosperity Party's military units, recently deployed from training camps, are reportedly disintegrating en route to the battlefield. Despite efforts by Prime Minister Abiy Ahmed's government to mobilize forces from across the country, many units are abandoning their posts. At least 85 soldiers reportedly defected in a single day—some joining Fano, others simply deserting. Sources confirm that most lacked proper combat preparation and were already planning to withdraw. The regime's reliance on rushed deployments has backfired, exposing deep cracks in its military structure.

📚 Education Resumes After Two-Year Disruption

After a two-year interruption, school registration has resumed across multiple fano-controlled districts. Based on AFPO's commitment, communities are mobilizing to restore education through public dialogue, school repairs, and student enrollment. Strong support and enthusiasm have been observed from students, parents, and teachers. However, some schools facing severe damage are calling for broader collaboration beyond local efforts, seeking support from partner organizations to ensure sustainable recovery.





❖ **የአገዛዙ ሠራዊት ከጦር ሜዳ ሽንፈት መልስ ንፁሃንን መግደሉን እንደቀጠለ ነው።**

ፀረ-አማራ የሆነው አብይ መራሹ ጨፍጫፊ ሠራዊት በየቀኑ በሚደረግ ውጊያ በሚደርስበትን ሽንፈት በየቤቱ እየገባ መዝረፍ፣ ማውደምና የፍልሚያው አካል ያልሆኑትን ንጹሃንን ዛሬም እንደ ትናንቱ በየቤታቸው መግደሉን ቀጥሏል። ለአብነትም ባሳለፍነው ሳምንት በሸዋ ጠቅላይ ግዛት አንፆኪያ ገምዛ ወረዳ ብቻ አርሶ አደር እሸቴ ዳመነ፣ ተማሪ ዋሱ እሸቴ ዳመነ፣ ወጣት ባሳዝን ጌቱ፣ ወጣት ሻምበል በቀለ፣ አርሶ አደር ሰሜ መንግስቴ፣ ህጻን ተመስገን ወሰኔ፣ ተማሪ ሸዋ ወሰኔ፣አርሶ አደር ታደሰ ጀማነህ እንዲሁም ጎንደር ጠቅላይ ግዛት እብናት ወረዳ ላይ ዝናብ አዲሴ፣ ሺመላሽ እሸቱ፣ ሙሉቀን አስማማው፣ ደሳለኝ ገብሬ፣ ወረታው በላቸው፣ አማረች አበጄ፣ ሙላት አድማስ በግፍ የተረሸኑ ሲሆን ቢተው ጌጡ፣ እናንየ አራጋው፣ መ/ር መሰሉ አማረ፣ ዳዊት ጌታሰው፣ ገብርዬ ጌጤነው፣ ውዲቱ ጺጋዬና አባቷ አቶ ጺጋዬ፣ ጥሩዬ ታደሰ ከባድ ቁስለኛ ሆነዋል። በጉና በጌምድር ወረዳ መ/ር ተመስገን ጌጤን ክምር ድንጋይ ከተማ አደባባይ አውጥተው የረሸኑ ሲሆን በተጨማሪም ወጣት ጌታሰው መኮነን፣ታደሰ አያሌው፣ አሰፋ ደሴ(አትሌት)፣ ካሳየ ብርሃን፣ ስራው መንግስቴ፣ ተስፋለም ልብሱ (የ9 ወር ነፍሰጡር) በአገዛዙ ወታደር በግፍ ተገድለዋል። በተጨማሪም በርካቶች ቁስለኛ ሆነው በህክምና ላይ ይገኛሉ። ስማዳ ወረዳ ላይ ወጣት ፍታለው አጥናፉ፣ አርሶ አደር ጌታሰው ገላው፣ አርሶ አደር ጨመረ አመኑ፣ አርሶ አደር ቢራራ አመኑ እንዲሁም ሰዴ ሙጃ ወረዳ ላይ አርሶ አደር ግዛቸው እና ልጃቸው ያብባል ግዛቸው ባሳለፍነው ሳምንት በአገዛዙ በግፍ ተገድለዋል። በላይ ጋይንት ወረዳ ተክሌ አበባው፣ ጌታ ዳኛው፣ አደራጀው ጌታ፤ ታች ጋይንት ወረዳ ላይ ጌታሰው ገላውና ፍታለው አጥናፉ በጭካኔ ተገድለዋል። ወሎ-ቤተ አማራ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ካሳ አለምነው፣ መምሬ ደስ ይላል፣ ወንዴ ደስ ይላል፣ መካሻው ገሰሰ፣ ደሳለኝ አለቤ የተባሉ አርሶ አደሮችን የአገዛዙ ሠራዊት በግፍ ጨፍጭፎ ገድሏል።

⚔️ Regime army has continued to avenge its loss on civilians

The Regime's army has continued its killing of innocent people in response to battlefield defeats. The anti-Amhara Abiy-led oppressive army continues to enter and destroy homes daily, killing innocent people who are not part of the conflict, just as it did yesterday. For example, in the past week alone, in the Shewa region, in the Antsokiya Gemza district, farmers like Eshete Damene, student Wasu Eshete Damene, youth Basazin Getu, youth Shambel Bekele, farmer Seme Mengiste, child Temesgen Wesene, student Shewa Wesene, farmer Tadesse Jemaneh, and in the Gondar region, in the Ebnat district, Zinab Adise, Shimelash Eshetu, Muluken Asmamaw, Desalegn Gebre, Woreta Belachew, Amarech Abeje, Mulat Admas, and others have been killed by the oppressive army. Additionally, in the Guna Begemdr districts, teacher Temesgen Getie was murdered at Kemer Dengay town square, and youth Getasew Mekonnen, Tadesse Ayalew, athlete Assefa Desse, Kasaye Birhan, Sraw Mengiste, Tesfalem Libsu (a 9-month pregnant woman) have been killed by the oppressive army. Furthermore, many others are severely injured and receiving medical treatment. In the Samada district, youth Fitalew Atnafu, farmer Getasew Gelaw, farmer Chemere Amenu, farmer Birara Amenu, and in the Sede Muja district, farmer Gizachew and his son Yabibal Gizachew have been killed by the oppressive army in the past week. In the Lay Gayint district, Tekle Abebaw, Geta Dagnaw, Aderajew Geta, and in the Tach Gayint district, Getasew Gelaw and Fitalew Atnafu have been killed in the chaos. In the Wollo-Bete Amhara region, Kasa Alemnew, Memre Desyilal, Wonde Desyilal, Mekashaw Gessesse, Desalegn Alebe, and other farmers have been brutally killed by the oppressive army.

# በምስሎች In Pictures











